# ወጪን በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣልዩ መመሪያ

# ቁጥር 24/2012 ዓ.ም.

# ***መግቢያ***

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የሚያስተዳድራቸው የበጎ አድራጎት ድርጅትቶችለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለሚሰጡት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎትተመጣጣኝ ዋጋ በማስከፈል በበጎ አድራጎት ስራ ላይ ለተሰማሩ ወይም ለሚሰማሩ ግልጽ እናወጥነት ያለውየአሰራር ስርአት መዘርጋትናዘለቄታ ያለው አገልግሎት ለመስጠትሲሆን ይህንን ስርዓት ዘርግቶ የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ የሚሠጡትን አገልግሎት ለማሳለጥ እና ለመደገፍ ይህ መመሪያ በኤጀንሲው ተዘጋጅቷል፡፡

## ***የልዩ መመሪያው አስፈላጊነት***

ተጠቃሚውን ህብረተሰብ ወጪንእንዲጋራበማድረግ አገልግሎት የሚሰጡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን አስተዳደር ከገቢ ማስገኛ መመሪያ ቁጥር 7/2004 በተለየ ሁኔታ መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና በአፈጻጸምና አስተዳደር ሂደት ላይ ያጋጠመውን ችግር ለመፍታትእንዲሁም ክትትልና ድጋፍለመስጠት ራሱን የቻለ የማስፈጸሚያ ልዩ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ለማጎልበት ወጪን በመጋራት የተግባሮቻቸውን ቀጣይነት የሚያግዝ የአሰራር ልዩ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የበጎ አድራጎት አገልግሎቶችን ወጪ በመጋራት ማከናወን የገቢ ማስገኛ ሥራ ተደርጎ እንዳይቆጠርና በንግድ የስራ ዘርፍ እንዳይመደቡ ለማድረግ ግልጽ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰበዉክፍያ ተመልሶ ለበጎ አድራጎት ተግባር እንዲውል እና ዘለቄታ እንዲኖረው የተለየ ስርዓት ለመዘርጋትበማስፈለጉ፤

ሙሉ በሙሉ በነፃ የሚሰጥ የበጎ አድራጎት አገልግሎት በኅብረተሰቡ ላይየሚፈጥረውን የጠባቂነት፣ ተመጽዋችነት እናጥገኝነትተጽዕኖ ደረጃ በደረጃ ከመቀነስጎን ለጎን የህብረተሰቡን የባለቤትነት መንፈስ ለማጎልበት በመታቀዱ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችተግባራቸውንከተጠቃሚው ኅብረተሰብበጉልበትእና በዓይነት በሚደረግ አስተዋፅኦ ወይም ወጪ በመጋራት የሚያከናውንበትን አሰራር መደገፍ፤ ማበረታታት እናክፍተቶችን ለማረም ግልጽ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር

621/2001 አቀንጽ 9(4)፣አንቀጽ **6/1/ቸ** እና በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ **34**በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

## አንቀጽ 1

## አውጪው አካል

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 9(4) ፣ አንቀጽ 6/1/ቸ እና በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 34 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 2

## አጭር ርዕስ

ይህ ልዩ መመሪያ ወጪን በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ የወጪ መጋራት ልዩ መመሪያ ቁጥር 24/2012ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 3

### ትር□ሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠውካልሆነ በስተቀር በዚህ ልዩ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 እና በደንብ ቁጥር 168/2001 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በዚህ ልዩ መመሪያ ውስጥ፡-

1.“የወጪ መጋራት“ማለት የበጎ አድራጎትድርጅቶችለሚሰጡት አገልግሎት በተሰጠቸው ፍቃድና ዓላማቸው መሰረት ተግባራቸውን ለማከናወንእንዲሁምየበጎ አድራጎት አገልግሎታቸውን በዘላቂነት ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ ከህብረተሰቡበጉልበትእና በዓይነትበሚያገኙት አስተዋጽኦ ወይም ወጪን በመጋራትአቅም ለሌላቸው በነጻ የበጎ አድራጎት ድጋፋቸውን ከመስጠት ጎን ለጎንለሰጡት አገልግሎት ከሚያስፈልገው ወጪከ25% ያልበለጠውን ከተጠቃሚው ኅብረተሰብ የሚጋሩበትየአሠራር ሥርአት ማለት ነው፡፡

2.¨ፈቃድ¨ማለትከተጠቃሚው ከኅብረተሰብበጉልበት እናበዓይነት በሚያገኙት አስተዋጽኦ ወይም ወጪንበመጋራት አገልግሎት ለሚሰጡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችየገቢ ማስገኛ

ፍቃድ ማውጣት ሳያስፈልግ ተግባራቸውን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ የሚገልጽከኤጀንሲውበጽሁፍ የሚሰጥ ነው፡፡

አንቀጽ 4

የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ ልዩ መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆነው ከኢፌዲሪ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ፍቃድ አውጥተውነገር ግንለሚሰጡት አገልግሎትየጉልበት ወይምየዓይነት አስተዋጽኦ ወይምወጪ በመጋራትየበጎ አድራጎትተግባራት ላይ የተሰማሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችሆኖ፡-

ሀ.ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤

ለ.በአንድ ክልል ብቻ የሚሰሩ ቢሆንም የውጪ ሀገር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች፤

ሐ.በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

መ/ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ልዩ መመሪያ በማህበራት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2/ ይህ ልዩ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከኤጀንሲው የገቢ ማስገኛ ፍቃድ አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ያሉ እንድሁም ወደ ፊት በንግድ ሥራ ተሠማርተው የበጎ አድራጎት አገልግሎት ለመስጠት በሚፈልጉየበጐ አድራጐት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ቢኖርም ከዚህ በፊት የገቢ ማስገኛ ፍቃድ አውጥተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩትና በዚህ ልዩ መመሪያ ለመተዳደር በማስረጃ የተደገፈ ጥያቄ ሲያቀርቡ እና ኤጀንሲው ሲያምንበት አገልግሎቱን ለማስቀጠል ኤጀንሲው በልዩ መመሪያው እንድካተቱ እንደገና ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በወጪ መጋራት ስለሚገኝ ገቢ አያያዝ እና አጠቃቀም

አንቀፅ 5

በወጪ መጋራት ስለሚገኝ ገቢ፤

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተጠቃሚዎች በወጪ መጋራት መልክየሚሰበስበውን ክፍያ ከሌሎች ገቢዎች በመለየት ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡

2/በወጪ መጋራት የሚሰበሰበው ገቢ ለተሰጠው አገልግሎት ከሚያስፈልገው ጠቅላላ ወጪ በመቶኛ ተሰልቶ ሲታይ ከሃያ አምስት በመቶ ያልበለጠ መሆን አለበት ፡፡

አንቀጽ 6

በወጪ መጋራት ስለሚገኝ ገቢ አጠቃቀም፤

1/ማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅትበወጪ መጋራት ያገኘውን ገቢ ድርጅቱ አገልግሎቱን ለማጠናከር ፍቃድ ካገኘበት አላማጋር በቀጥታ ተያያዥነት ላላቸው ተግባራት ማዋልአለበት።

2/የበጐ አድራጎት ድርጅቱ በወጪ መጋራት ያገኘው ገቢ ለሌሎችየድርጅቱ አስተዳደራዊ ወጪዎች መሸፈኛነት ሊውል አይገባም።

3/ ከህብረሰቡ በወጪ መጋራት የሚሰበሰበውገንዘብ ለበጐ አድራጎት ድርጅቱ አባላት ሊከፋፈል አይችልም።

# ክፍል ሦስት

## ስለ ወጪ መጋራትፍቃድ አሰጣጥናይዘት

አንቀፅ 7

ስለ ወጪ መጋራትፍቃድ አሰጣጥ

1/ በነጻ ከሚሰጠው የበጎ አድራጎት አገልግሎት በተጨማሪበወጪ መጋራትከተጠቃሚው ኅብረተሰብ ክፍያ በመሰብሰብ የበጎ አድራጎት አገልግሎት ለመሥጠት የሚፈልግ የበጐ አድራጎት ድርጅትጥያቄውን ለኤጀንሲው በፅሁፍ ማቅረብ አለበት።

2/ በወጪ መጋራትየበጎ አድራጎት አገልግሎት ለመሥጠትለኤጀንሲው የሚቀርብ ጥያቄ በበጐ አድራጐት ድርጅቱ ቦርድየፀደቀ ሆኖ የሚከተሉትን ማካተት ይገባዋል።

ሀ/ የበጎ አድራጐት ድርጅቱ የተቋቋመበትና ለሚሠጠው አገልግሎት ወጪ ለመጋራት የተፈቀደለትን ዓላማ፤

ለ/ የበጎ አድራጐት ድርጅቱ ስም ፣ አድራሻ እና የምዝገባ ሰርተፍኬት ኮፒ፤

ሐ/ የአገልግሎት ክፍያ አንድ መቶ ሃምሳ ብር እንዲሁም

መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተጠቃሚዎች ሊጋራ ያቀደዉ ወጪ ከ25% ያልበለጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ፤

ሠ/ በወጪ መጋራት ተግባር ላይ አዲስ ለመሰማራት የሚፈልግ የበጎ አድራጐት ድርጅት ግልፅና ዝርዝር ዕቅድ አያይዞ ማቅረብ አለበት።

ረ/ ሆኖም በጎ አድራጎት ድርጅቱ ልዩ መመሪያው ከመውጣቱ አስቀድሞበወጪ መጋራት መልኩ አግልግሎት እየሰጠየቆየ ከሆነ የተሰማራበትን የሥራ ዘርፍበመከለስ ፣ ተጠቃሚውን ኅብረተሰብ በማወያየት ያገኘውን ድጋፍና አገልግሎቱን የሚሰጥበት አከባቢ አስተዳደር እርከን የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ አያይዞ ለኤጀንሲው በፅሁፍ በማሳወቅ ማስፈቀድ አለበት።

## አንቀጽ 8

## ፍቃድ ሰጪው አካል

1/ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያ ነዋሪዎች በጐ አድራጐት ድርጅቶችበወጪ መጋራት አገልግሎት የመስጠት ተግባር ላይ እንዲሰማሩመስፈርቱን አሟልተው ሲቀርቡ ከሚመለከተው የዘርፍ አስተዳደር ጋር በመመካከር በክትትልና ድጋፍ ከፍተኛ ባለሙያ አማካይነት ፍቃዱ በ10 ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

2/ የውጭ በጎ አድራጐት ድርጅቶች በወጪ መጋራት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ለሚቀርብጥያቄ ማመልከቻው በቀረበበት በ15 ቀናትውስጥ ከሚመለከተው የዘርፍ አስተዳደር ጋር በመመካከርበክትትልና ድጋፍ ከፍተኛ ባለሙያዎች ተጣርቶ መስፈርቱን አሟልተውሲቀርቡ በክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር አማካይነት ፍቃዱ ይሰጣል፡፡

## አንቀፅ 9

## የወጪ መጋራትፍቃድ ይዘት

የወጪ መጋራት ተግባርከኤጀንሲው በጽሁፍ የሚሰጥ ፍቃድ ሆኖ የሚከተሉትን የያዘ መሆን አለበት፡፡

1/ ከኤጀንሲው በፅሁፍ የሚሰጥ ፍቃድ፤

2/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ስምና አድራሻ፤

3/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ እንዲሰማራ የተፈቀደለት የአገልግሎት አይነት፤

4/ ፍቃዱ የተሰጠበት ጊዜ፤

## አንቀፅ 10

## የወጪ መጋራት ስራ ፍቃድ ስለሚቀጥልበት ሁኔታ

የወጪ መጋራቱ ሥራ ፍቃድ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በልዩ መመሪያው መሠረት ለአገልግሎቱ ዘላቂነት  ከሃያ አምስት በመቶ ያልበለጠውን ከተጠቃሚው ኅብረተሰብ በመጋራት እስከተንቀሳቀሰ ድረስ በየአመቱ ልዩነቱን ለኤጀንሲው በማሳወቅ አገልግሎቱን መቀጠል ይችላል ፡፡

## አንቀጽ 11

## የወጪ መጋራትፍቃድ ስለሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱወጪ በመጋራት አገልግሎት ለመስጠት የሚቀርብ ጥያቄ ከተመዘገበበት፣ ፍቃድ ከተሰጠበትዓላማና የሥራ መስክ ጋርቀጥተኛ ባልሆኑ ተግባሮች ላይ ለመሰማራት ሲሆን፤

2/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ከተመዘገበበት እና ፍቃድ ካገኘበት ዓላማ ውጭ ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ ከኤጀንሲው የፅሁጽ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው አንድ ዓመት ያልሞላውመሆኑ ሲረጋገጥ፣

3/ የወጪ መጋራቱ ጥያቄ ከ25% በላይ ሲሆን፤

4/ኤጀንሲውም የክልከላ ደብዳቤውን በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጎ አድራጎት ድርጅት በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

<u>አንቀጽ 12</u>

<u>ስለ ወጪ መጋራት ፍቃድና ሌሎች ሁኔታዎች</u>

1/ በወጪ መጋራት ተግባር ላይ የተሰማራ የበጎ አድራጐት ድርጀት ከኤጀንሲው በፅሁፍ ፍቃድ ካገኘ በኂላ ለሚመለከተው የመንግስት አካልና ለተጠቃሚው ህብረሰብከወጪ መጋራቱ ከ25% በላይ ስላለማግኘቱ የኦዲትና የክንዉን ሪፖርት የማቅረብና የማስረዳት ግዴታ አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1የተመለከተውእንደተጠበቀ ሆኖ እስከ 25%ተብሎ የተጠቀሰው አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት በሚሰጣቸው አገልግሎቶችጥቅል ሪፖርት እንጂ ለእያንዳንዱ አገልግሎትየተናጠል ሪፖርት እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም፡፡

3/ በዚህ ልዩ መመሪያ ተራ ቁጥር 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወጪ መጋራትፍቃድ ያገኘማንኛውም የበጎ አድራጐት ድርጅት ከወጪ መጋራቱ ዉስጥ ከ25%በላይ የሚሰበስብመሆኑ ሲረጋገጥ ኤጀንሲው ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ ስረዛ የሚያደርሱ እርምጃዎችን ሊወሰድ ይችላል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>በወጪ መጋራትስለሚሰበሰብ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም</u>

<u>አንቀጽ 13</u>

<u>የወጪ መጋራት ሂሣብ መዝገብ</u>

1/ በወጪ መጋራት ተግባር ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ከወጪ መጋራትለሚሰበስበውገንዘብየተለየ የሂሣብ መዝገብ መያዝ አለበት፡

2/ በወጪ መጋራት ተግባር ላይ የሚሳተፍ የበጐ አድራጐት ድርጅት የሚሰበስበስውን ገንዘብ በተለየ የባንክ ሂሳብማስቀመጥአለበት፡፡

3/ በወጪ መጋራት ተግባር ላይ የሚሳተፍ የበጐ አድራጐት ድርጅት የባንክ ሂሣብ ለመክፈት ከኤጀንሲው ፍቃድ ማግኘት አለበት፡፡

## አንቀጽ 14

## ከወጪ መጋራት የሚገኝ ገንዘብ አጠቃቀም

ከወጪ መጋራት  የሚገኝ ገንዘብ ሙሉ በሙሉየበጐ አድራጐት ድርጅቱ ለሚሰጠው አገልግሎትና ፍቃድ ለተሰጠው ዓላማ ብቻ መዋል አለበት፡፡

## አንቀጽ 15

## የወጪ መጋራትአስተዳደር

ከወጪ መጋራት የሚሰበሰብ ገንዘብን  በተመለከተ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለዚሁ ተግባር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የየዕለት እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውን ባለሙያ ሊመደብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16

## ስለ ወጪ መጋራት ሪፖርት አቀራረብ

1/ የበጎ አድራጐት ድርጅቱከወጪ መጋራትየሚያገኘውን ገንዘብአጠቃቀም የሚያሳይ ግልፅ ዓመታዊ የኦዲትና የክንውን ሪፖርት በአዋጁ አንቀጽ 80 በተደነገገው መሠረትበርዕሥ በመለየት ከዋናው ሪፖርት ጋር አካትቶ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲትና የክንውን ሪፖርት አቀራረብና ይዘትን በተመለከተ የአዋጁ አንቀፅ 77-81 እና አንቀፅ 83 ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 17

## የወጪ መጋራት ፍቃድስለ መሰረዝ

1/ ማንኛውም በጐ አድራጎት ድርጅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ሆነ ብሎ የፈጸመ እንደሆነ ኤጀንሲው እንደ ህጉ ጥሰት ክብደት ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ ስረዛ የሚያደርሱ እርምጃዎችን ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሀ\ ለሚሰጣቸው የበጐ አድራጐት አገልግሎት ፍቃድ ሳያገኝ የወጪ መጋራት ክፍያ ሲሰበስብ  ከተገኘ ፤

ለ/ በዚህ ልዩ መመሪያ አንቀፅ 6 የተደነገገውን በመጣስ በወጪ መጋራት የተሰበሰበውን ገንዘብ ለአባላት ሲያከፋፍልና ለሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች ሲያውል ከተገኘ፤

ሐ/ በዚህ ልዩ መመሪያ አንቀጽ 13 የተደነገገውን በመጣስለሚሰበስበው ገንዘብ የተለየ የሂሳብ መዝገብ ካልያዘ ፤

መ / የሥራ እንቅስቃሴውን ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብና ለመንግሥት አካል በተጠየቀ ጊዜ ለማሳየት /ለማቅረብ/ ፈቃደኛ ካልሆነ ፤

ሠ/ የበጐ አድራጎት ድርጅቱከኤጀንሲዉ ፍቃድ ካገኘበት አገልግሎት ዉጭባሉ ተግባራት ወጪ መጋራትንሽፋን በማድረግክፍያዎችን ሲሰበስብ ከተገኘ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱ ወንጀል ነክ ከሆነ በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3/ ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ለበጎ አድራጐት ድርጅቱ በወጪ መጋራት እንዲሳተፍ የሚሰጠው ፍቃድ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነት ሲያከትም አብሮ ቀሪ ይሆናል፡፡

አንቀፅ 18

የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት

1/ በዚህ ልዩ መመሪያ አንቀፅ 8 (1) በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው የበጎ አድራጐት ድርጅት በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለክትትልና ድጋፍዳይሬክተር ቅሬታውን በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው በጎ አድራጎት ድርጅትበ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላል፡፡

3/ ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታው ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 19

የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ከዚህ በፊት ከኤጀንሲውፍቃድ ሳያገኙ የወጪ መጋራት አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይየተሰማሩ በጐ አድራጐት ድርጅቶች ወጪ በመጋራት ለሚሰጡት አገልግሎት ይህልዩ መመሪያከጸናበት እስከአንድ አመት ባለው ጊዜ አስፈላጊውንፈቃድ ከኤጀንሲው በጽሁፍ ማግኘት አለባቸው፡፡

አንቀጽ 20

ልዩ መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን ልዩ መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 21</u>

<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህልዩ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያምሆነ ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነትአይኖረውም፡፡

<u>አንቀጽ 22</u>

<u>ልዩ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ልዩ መመሪያ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ ፀድቆ ከወጣበት ከ----- እስከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መሠረት ገ/ማርያም ተክሉ

የኢፌዲሪ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

<u>አዲስ አበባ</u>